**<u>የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ</u>**

**<u>አመል ማይክሮፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር</u>**

**<u>የባለአክሲዮኖች ፲ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ</u>**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ እና አንቀጽ 370 መሠረት አመል ማይክሮፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች ፲ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ታህሳስ ፲፱ ቀን 2017 ከጠዋቱ 2:00 ጀምሮ በአዲስ አበባ ለገሃር አከባቢ በሚገኘው ራስ ሆቴል አዳራሽ ይካሄዳል።

በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. **<u>ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች</u>**

   1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡- አ/አ ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 05፣ የቤት ቁጥር አዲስ፣

   ድረ-ገጽ፡ https://amalmicrofinance.com

   1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- MFI/056/2023

   1.3 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ፡- <u>67,762,000.00</u>

   1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ፡- <u>34,533,265.00</u>

2. **<u>የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች</u>**

   2.1 እ.ኤ.አ እስከ ታህሳስ 20/2024 የተፈጸሙ የአክሲዮን ዝውውሮችን እና ሽያጮችን ማጽደቅ፣

   2.2 እ.ኤ.አ የ2023/2024 ሂሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

   2.3 እ.ኤ.አ የ2023/2024 ሂሳብ ዓመት የውጪ ኦዲሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

   2.4. የነባር ውጪ ኦዲተሮች በአዲሱ የውጭ ኦዲተሮች መመሪያ መሠረት የሥራ ቀጣይነትን ላይ መወያየትና መወሰን

   2.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን የ2024/25 ወርሃዊ አበል መወሰን፣

3. **<u>ማሳሰቢያ</u>**

3.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በማህበሩ ዋና መ/ቤት ወይም ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾም እና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተካፋይ ለመሆን እና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

3.2 ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውን እና ኮፒ በመያዝ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እንገልጻለን።

አመል ማይክሮፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ